# የብፁዕ አቡነ ሚካኤል

## የሕይወት ታሪክ ።

ይህ መጽሐፍ፡ በአምስቱ የመከራ ዘመናት በኢየሩሳሌም የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የጐንደር ጳጳስ ለነበሩት ለብፁዕ አቡነ ሚካኤል በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ያሠሩት ሐውልት ለሚገለጥበት ለጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ፡ ም፡ መታሰቢያ ሆኖ ታተመ ።

አዲስ አበባ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ. ም.

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org



የጐንደር ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ።

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ ፤

የበጌ ፡ ምድርና ፡ የስሜን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ጳጳስ ፡ የነበሩትና ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ የተለዩት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ከሕፃንነት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ጀምሮ ፡ ቅዱሱ ፡ ሰውነታቸው ፡ በመቃብር እስከተወሰነበት ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በመማር ፤ በማስተማር ፤ በጾም ፤ በጸሎት ፤ በብሕትውና ፤ በጠቅላላውም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ የታወቁና የተመሰገኑ ፡ እውነተኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ነበሩ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ብፁዕ ፡ ቅዱስ ፡ ቢሆን ፡ በሞት ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ኃይል ፡ መያዝ ፡ የማይቀርለት ፣ ስለሆነ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ፡ ሚካኤል ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ጥቅምት ፡ ፴ ቀን ፣ ከፈጣሪያቸው ፡ በሞት ፡ ተጠርተው ፡ በግሸን ፡ ማርያም ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ በክብር ፡ ተቀበሩ ።

ምንም ፡ መቃብራቸው ፡ በግሸን ፡ ማርያም ፡ ቢሆን፡ የአባትነታቸውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያስታውሰው ፡ በማለት ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፤ ርዳታና ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፤ እንዲሁም ፡ በንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብና ፡ በአምስቱ ፡ የመከራ ፡ ዘመናት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የስደት ፡ ተካፋዮቻቸው ፡ በነበሩት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተዋጽኦ ፡ በመንበረ ፡ ፀባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ ውስጥ ፡

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## መ ግ ቢ ያ፤

በስማቸው ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ቆመላቸው ።

ለሐውልቱም ፡ ወጭ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ $ 6702. 50 (ስድስት ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ከሃምሣ ፡ ሣንቲም) ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ሐውልቱ ፡ በሚገለጥበት ፡ በዕለተ ፡ ዕረፍታቸው ፡ ጥቅምት ፡ ፬ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. ፡ ይህ ፡ የሕይወት ፡ ታሪካቸውንና ፡ ዜና ፡ ሞታቸውን ፡ የሚገልጸው ፡ መጽሐፍ ፡ የመታሰቢያውን ፡ በዓል ፡ ለማክበር ፡ በሐውልቱ ፡ ዙሪያ፡ የተሰበሰቡት ፡ ይመለከቱት ፡ ዘንድ ፡ ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ በስደተኞቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ታተመ ።

## በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩ ፡ ስደተኞች ።

### ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ማሠሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ያዋጡ ።

| ተራ ቁጥር | ስ ም ፡ | የገንዘቡ ልክ ብር |
|---|---|---|
| 1 | ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ | 1000 |
| 2 | ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ | 1000 |
| 3 | ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ | 500 |
| 4 | ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ | 500 |
| 5 | ልዕልት ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ | 500 |
| 6 | ልዕልት ፡ መድፈሪያሽ ፡ ወርቅ ፡ አበበ ፡ | 300 |
| 7 | ልዕልት ፡ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ ገብረ ፡ ሩፋኤል ፡ | 400 |
| 8 | ልዑል ፡ ደጃዝማች ፡ አሥራተ ፡ ካሣ ፡ | 200 |
| 9 | ወይዘሮ ፡ የምሥራች ፡ እምሩ ፡ | 100 |
| 10 | ልዕልት ፡ ዓይዳ ፡ ደስታ ፡ | 200 |
| 11 | እመቤት ፡ ሆይ ፡ ኂሩት ፡ ደስታ ፡ | 100 |
| 12 | እመቤት ፡ ሆይ ፡ ሶፍያ ፡ ደስታ ፡ | 100 |
| 13 | እመቤት ፡ ሆይ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ደስታ ፡ | 100 |
| 14 | ኮማንደር ፡ እስክንድር ፡ ደስታ ፡ | 200 |
| 15 | ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ መንገሻ ፡ | 100 |
| 16 | ወይዘሮ ፡ ማርታ ፡ እምሩ ፡ | 100 |
| 17 | ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ | 600 |
| 18 | ኰሎኔል ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ | 200 |
| 19 | ፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ከበደ ፡ | 300 |
| 20 | ልጅ ፡ ሚካኤል ፡ እምሩ ፡ | 200 |
| 21 | ደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ | 200 |
| 22 | ልጅ ፡ መንበረ ፡ ያየህ ፡ ይራድ ፡ | 100 |
| 23 | ፊታውራሪ ፡ ረታ ፡ ገብረ ፡ አምላክ ፡ | 100 |
| 24 | በጅሮንድ ፡ አባትሁን ፡ | 200 |

www.ethiopianorthodox.org

## ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ጳጳስ ፡ ዘጎንደር ፤

ይህ ፡ ዓለም ፡ መቆያ ፡ እንጂ ፡ ለዘለዓለም ፡ መኖሪያ ፡ አለመሆኑን ፡ በማወቅ ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ ከተወለዱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞታቸው ፡ ድረስ ፡ የገድልን ፡ ጎዳና ፡ በመከተል ፡ የሚፈጽሙት ፡ መንፈሳዊ ፡ ተጋድሎ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ዋጋቸውም ፡ በዚያው ልክ ፡ ነው ።

ምንም ፡ ሥጋ ፡ ቢለብሱ ፡ ንጽሕናቸውና ቅድስናቸው ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ስለሆነ ፡ ጸሎታቸው ፡ ይጠቅማል ። ትሩፋታቸውም ፡ ያጸድቃል ። በዚህ ፡ መሠረት፡ የኢትዮጵያ ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ መሆናቸው ፡ ታውቋል ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ናቸው ።

የጎንደር ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፡ ጳጳስ ፡ ብፁዕ አቡነ፡ ሚካኤል ፡ (የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ መምህር ፡ ክፍለ ፡ ገሪማ) ፡ በ፲፰፻፸፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግንቦት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ከመሬጌታ ፡ ወልደ ፡ ኪዳንና ፡ ከወይዘሮ ፡ ደስታ ፤ ግሸን ፡ ላይ ፡ ተወለዱ ።

በዚሁ ፡ ዓመት ፡ የጥምቀታቸው ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመው ፡ ሰኔ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ስለነበረና ፡ በዚህ ፡ ቀን የአባ ፡ ገሪማ ፡ በዓል ፡ ስለዋለ ፡ ስማቸው ፡ ክፍለ ፡ ገሪማ ፡ ተብሏል ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሁለቱ ፡ ቅዱሳን ፡ በስም ፡ አንድ ፡ የሆኑትን ፡ ያህል ስለአባ ገሪማ ፡ «አስኬማ ከኒ ፡ አልባቲ ፡ ሙስና» ፡ ተብሎ ፡ በቅዱስ ፡ ያሬድ፡ እንደተነገረው ፤ በምንኵስናቸው ፡ ፍጹምነት ፡ ሁለቱም፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ለትምህርት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜም ፡ በዚሁ ፡ በተወለዱ በት ፡ አገር ፡ በግሸን ፡ የንባብና ፡ የዜማ ፡ ትምህርት ፡ ተማሩ ፤ ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ሜዳ ፡ ሒደው ፡ ቅኔ፡ ተማሩ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በ፲፰፻፺፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዚ ያው ፡ በበሩ ፡ ሜዳ ፡ ከመምህር ፡ ደስታ (ኋላ ፡ አቡነ፡ አብርሃም) በሦስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳትን ፡ አጠኑ ።

ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሒደው ፡ ከአለቃ ፡ ዘዮሐንስ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተምረው ፡ ዐወቁ ። ከዚ ያም ፡ ወደ ፡ መከነ ፡ ኢየሱስ ፡ ተመልሰው ፡ ከአለቃ፡ ወልዱ ፡ ሚካኤል ፡ እንደገና ፡ ሐዲሳትን ፡ ዘለቁ ።

ቀጥሎም ፡ ከደረስጌው ፡ ከአለቃ ፡ ብሩ ፡ የ፲፬ቱን፡ መጻሕፍተ ፡ ቅዳሴ ፡ ትርጓሜ ፡ ደህና ፡ አድርገው አጠኑ ። የጥንቱ ፡ የቅዳሴ ፡ ንባብ ፡ ዋናው ፡ አብ ነቱ ፡ የሚገኘው ፡ ከእሳቸው ፡ ነበር ። ብፁዕ ፡ አቡነ፡ ሚካ ኤል ፡ «ዘእምንዕሱ ፡ ሕይወቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ እግዚአብ ሔር» ፡ በተባለው ፡ መሠረት ፡ የተሳለሙዋቸውና ፡ ጸሎት ፡ የጸለዩባቸው ፡ ገዳማት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።



ጐንደር ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ በዋልድባ ፤ በመንዳባ ፤ በደብረ ፡ ገሊላ ፤ በሌሎቹም ፡ በደሴተ ፡ ጣና ፡ ገዳ ሞችና ፡ በሞጊና ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ጸሎት ፡ አድርሰዋል ። በየቃላላቆቹም ፡ አድባራት ፡ በደሴተ ፡ ጣና ፡ በሞጊና ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ከየሊቃውንት ፡ የተደረሱትን ፡ የዓይን፡ መጻሕፍቶችና ፡ አዋልዶችን ፡ በመመርመር ፡ ምሁር ነታቸውን ፡ የተሟላ ፡ አድርገዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከደቀ ፡ መዝሙርነት ፡ ወደ ፡ አስተማ ሪነት ፡ ተዛውረው ፡ በ፲፱፻፲ ዓ. ም የተማሯቸውን ፡ መጻ ሕፍት ፡ ማስተማር ፡ ጀመሩ ። በሚማሩበትና ፡ በሚያስተ ምሩበትም ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ አሳባቸው ፡ በመንፈሳዊነት፡ የተቃኘ ፡ ስለሆነ ፡ ኑሯቸው ፡ በሰጊድና ፡ በቀ ዊም ፤ በጸሎትና ፡ በትምህርት ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። በተ ለይም ፡ የቅዳሴ ፡ ትርጓማቸው ፡ ተፈላጊ ፡ ስለነበረ ፡ በጉባኤያቸው ፡ ብዙ ፡ ደቀ፡ መዛሙርት፡ ይገኙ፡ ነበር ። ከነ ዚሁም፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ አለቃ ፡ አፈወርቅ ፡ ዘለቀ ፡ ከእሳቸው ፡ ቅዳሴን ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ተምረው ፡ ሙሉውን ፡ ትርጓሜ ፡ ተርጕመው ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አቅርበው ፡ ታትሟል ። ይህም ፡ በነጠላ ፡ ትር ጉም ፡ ከተዘጋጀው ፡ ቅዳሴ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሁኖ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤልን ፡ ባለውለታነት ፡ ያሳስባል ።

በ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ. ም. ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ በደብረ ፡ ሊባ ኖስ ፡ የምንኵስና ፡ መዓርግ ፡ ተቀበሉ ፤ ወዲያው ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ የቅስና ፡ መዓርግ ፡ ተቀበሉ ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሔደው ፡ መቃብረ፡ ክርስቶስን ፡ ተሳለሙ ። በ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ. ም. በመስከረም ወር ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በገነተ ፡ ልዑል፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ በመንበረ ፡ ልዑል ፡ ቅዱስ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በማስተማርና ፡ በጸሎት ፡ ተፀምደው፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ ኖሩ ። በ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ. ም. በግርማ ዊነታቸው ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡ ታትሞ ፡ ለየአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ሁሉ ፡ የታደለውን ፡ የመጻ ሕፍተ ፡ ቅዳሴን ፡ ነጠላ ፡ ትርጓሜ ፡ ከግዕዙ ፡ ጋር ፡ በማ ስማማት ፡ አዘጋጅተው ፡ እንዲገለገልበት ፡ ተደርጓል ።

በመንበረ ፡ ልዑል ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ በጸሎት ፡ ጽሙድ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላ ይና ፡ የመጻሕፍተ ፡ ቅዳሴን ፡ ትርጉም ፡ ለቀረቡላቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ከማስጠናታቸው ፡ በላይ ፡ በሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ረገድ ፡ ቀሳውስትንና ፡ ዲያቆናትን ፡ በማሠልጠን፤ መጻሕፍትንም ፡ በማቃናት ፡ ሠርተዋል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የአንዳንድ ፡ ችግረኞችን ፡ ጉዳይ ፡ ለግርማዊነታ ቸው ፡ በማቅረብ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸውና ፡ ጃንሆይን ፡ እያመሰገኑ ፡ እንዲመለሱ ፡ አድርገዋል ።

መንግሥቱም ፡ ጽኑ ፡ ሰላም ፡ እንዲሆንና ፡ ለሕ ዝበ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሣህል ፡ ምሕረት ፡ እንዲወርድ ፡



ከፍ ፡ ባለ ፡ ትሩፋት ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ለሀገራቸው ፡ አበርክተዋል ።

ብፁዕ፡አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ የሚ ታያቸው ፡ ሁሉ ፡ ገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለሆነ ፡ ከፊታ ቸው ፡ ብሩህነት ፡ በቀር ፡ የጥርስ ፡ ፍልቅቅታና ፡ የቃል ፡ ጨዋታ ፡ አልነበራቸውም ።

ከጸሎት ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ደኅንነት ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ጽናትና ፡ ብዛት ፡ የሚናገረው ፡ ድርሳነ ፡ ማሕየዊ ፡ ስለነበረ ፤ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ቁመው ፡ ሲደግሙት ፡ መንፈሳዊ ፡ ሁናቴያቸው ፡ ሌላ ፡ ነበር ። በሰሙነ ፡ ሕማማትማ ፡ የነበራቸው ፡ ተመስጦ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ጉዳይ ፡ በፍጹም ፡ አስረስቷቸው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ የትውልድ ፡ አገራቸውን የግሸን ፡ ማርያምን ፡ ገዳም ፡ መምህርነት፡ ተሹመው ፡ በዚሁ ፡ ገዳም ፡ ፫ ዓመት ፡ እያስተማሩና ፡ የትሩፋታቸውን ፡ ሥራ ፡ እየፈጸሙ ፡ ኖረዋል ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ የተወለዱበትን ፡ አገር፡ ግሸንን ፡ በጣም ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ በል ደት ፡ ሀገርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብና ፡ የእመቤታችን ፡ ቤተ፡

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ፡ ባለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በመሆኑና ፡ በሥፍራው ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግማደ ፡ መስቀል ፡ የተቀበረበት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የግሽን ፡ አቀማመጥ፡ በወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሲሆን ፡ በተለይ ፡ የጐንደር፡ ጳጳስ ፡ ለነበሩት ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ የፈቀዱላቸው ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ይህ ፡ ሥፍራ ፡ የትሩፋታቸው ፡ ላብ ፡ የነጠበበት ፡ በመሆኑ ፡ መከነ ፡ ዕረፍታቸው ፡ በዚሁ ፡ ሆነላቸው ።

የጐንደር ፡ ጳጳስ ፡ ሆነው ፡ በተሾሙ ፡ ጊዜ ፡ ስመ፡ሚመታቸው ፡ ሚካኤል ፡ እንዲባል ፡ ለመፍቀዳቸው ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉት ። አንደኛው ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ይወዱ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ በግሽን ፡ አጠገብ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተዋል ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሺህ ፡ ፬፻፳፯ ዓ.ም ፡ የክርስቶስ ፡ ግማደ ፡ መስቀል ፡ «የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ መስቀሉን ፡ በመስቀሌ ፡ ላይ ፡ አኑረው» ፡ በማለት ፡ በአመለከተው ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ ግሽን ፡ ሔዶ ፡ መስከረም ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ ሲያርፍ ፡ ቦታውን ፡ ከባረኩትና ፡ በዓሉን ፡ ካከበሩት ፡ ጳጳሳት ፡ አንደኛው ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ ይባል ፡ ስለነበር ፡ ይህን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ፡ እንደሆነ ፡ ታውቋል ።



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ መስከረም ፡ ፳፩ ቀን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ስለሆነ ፡ በያመቱ ፡ ቀድሰው ፡ ለምእመናኑ ፡ ቊርባን ፡ አቀብለው ፡ ከዋሉ ፡ በኋላ ፡ እንግዶችን ፡ ለማስተናገድ ፡ የነበራቸው ተወክሮ ፡ ነግድ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ሰውንም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነበር ። የሚቀበሉት ፡ ቀለብ ፡ የሚያልቀው ፡ ለድኃ ፡ በመስጠትና፡ እንግዳን ፡ በመቀበል ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ እርግጥ ፡ ነው። በሹመትም ረገድ ፡ የገዳማት ፡ መምህር ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ጳጳስም ፡ ሁነው ፡ ሲሾሙ ፡ ፈቃድ ፡ አልነበራቸው ። በምልጃ ፡ ብዛት ፡ ነው ፡ የተሾሙት ።

የእመቤታችንም ፡ ፍቅር ፡ በጣም ፡ ይጸናባቸው ፡ ስለነበረ ፡ አርጋኖን ፡ ሲደግሙና ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፡ ሲያነቡ ፡ ስሟ ፡ በተነሣ፡ ቊጥር ፡ አድንኖ ፡ ርእስ ፡ ሲያደርጉ ፡ አይታክታቸውም ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ፡ም ፡ መስከረም ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ራይስ ፡ ተብለው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚገኙት በአራቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳማት ፡ ተሾሙ ። በኢየሩሳሌምም ፡ በነበሩበት፡ ጊዜ ፡ መንፈሳዊ ፡ አርበኛ ፡ ሆነውና ፡ የክርስቶስን ፡ ቃል ፡ ዋና ፡ መግሪያ ፡ አድርገው ፡ በዚያ ፡ በአምስቱ፡ ዓመት ፡ ስደተኞችን ፡ በመቀበልና ፡ በማጽናናት ፡ በራሳቸው ፡ በኩል ፡ የደረሰውን ፡ ፈተና ፡ በመታገሥና ፡ ለከሳሾቻቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በገለጠላቸው ፡ መሠረት ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ በመስጠት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሐዋርያነት ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ፈጽመዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

በእሳቸው ፡ ተጋድሎና ፡ መንፈሳዊ ፡ አርበኝነት ፡ ምክንያት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ አልተደፈረም ። ጸሎታቸው ፡ ሐፁረ ፡ እሳት ፡ ሆኖ ፡ የጠላትን ፡ ኃይል ፡ አግዶታል ፣ ቆራጥነታቸውም ፡ ምሽግ ፡ ሁኖ ፡ ጠብቆታል ።

መንፈሳዊነት ፣ ስሜታቸውን ፡ ስለማረከው ፡ ንግግራቸው ሁሉ ፡ በለዘብታና ፡ በዝግታ ፡ ነበር ። የሚያስቆጣ ፡ ነገር ፡ በገጠማቸው ፡ ቍጥር ፡ ትዕግሥታቸው የበዛ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ይገረምላቸዋል ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋውን ፡ ያርከፈከፈበት ፡ ረድኤታቸውም ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ።

ጊዜን ፡ ተከትሎ ፣ ባለጊዜን ፡ መስሎ ፣ ከእውነት ፡ ተፈናቅሎ ፡ ከመኖር ፡ ሞትን ፡ የሚመርጡ ፣ ሥጋቸውን ፡ ለነፍሳቸው ፣ ነፍሳቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በማስገዛት ፡ ቆራጥነት ፡ ያላቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ አርበኛ ፡ ነበሩ ።

በዚያ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢገኙ ፡ ኖሮ ፡ ያለጥርጥር ፡ ስለሃይማኖታቸውና ፡ ስለሚወዷት ፡ አገራቸው ፡ በሰማዕትነት ፡ በፋሽስት ፡ እጅ ፡ የሞትን ፡ ጽዋ ፡ በተቀበሉ ፡ ነበር ።

ጸሎት ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ እሮይ ፡ መባያ ፡ ዓረፍት ፣ መደገፊያ ፣ መቋሚያ ፡ አይዙም ። በመከከል ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ ቁመው ፡ ሕሊናቸው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሳይል ፡ በቀጥታ ፡ ከፈጣሪያቸው ፡ ጋር ዋይታ ፡



በማድረግ ፡ ላይ ስለሚገኙ ፡ ምንም ፡ ቢመጣ ፡ ምንም ፡ ቢናገራቸው ፡ የጸሎት ፡ መጽሐፋቸውን ፡ አያጥፏትም ። ቀኑን ፡ እንዲሁ ፡ ውለው ፡ ሌሊቱንም ፡ እንዲሁ ፡ ያድሩታል ። በእሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ዕንቅልፍ ፡ የሚቆጠረው ፡ እንዳልተፈጠረ ፡ ነው ።

እውነት ፡ ከነእምነቱ ፣ ምግባር ፡ ከነትሩፋቱ ያለው ፡ ከእሳቸው ፡ ጋራ ፡ ስለነበረ ፡ የሐሰት ፡ ስብከት ፡ አይበግራቸውም ፡ ነበር ።

ነፃነት ፡ ሲበደል ፣ ወገን ፡ ሲጐሳቆል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከዙፋኑ ፡ ሲታጣ ፣ የዱሮው ፡ ወግና ፡ ሕግ ፡ ሲሻር ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ለጊዜው ፡ ይድላኝ ፡ እንጂ ፡ የማይሉ ፡ ቅዱስና ፡ ብፁዕ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ።

በኢየሩሳሌም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ከፈጸሟቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ ጥቂቶችን ፡ እንደሚከተለው ፡ እንገልጻለን ።

ፋሽስቶች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከወረሩ ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለመያዝ ፡ የነበራቸውን ፡ አሳብ ፡ ለመፈጸም ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ያመጡባቸው ፡ ነበር ፣ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሐሰት ፡ ክስ ፡ አቅርበው ፡ ባገሩ ፡ ገዥዎችና ፡ በዳኞች ፡ ቃል ፡ አስጠሯቸው ። ወደ ፡ ክሱም ፡ ስፍራ ፡ ከመሔዳቸው ፡ በፊት ፡ ከነአማካሪዎቻቸውና ፡ በስደት ፡ ከዚያ ፡ ከነበሩ ፡ ከኢ

www.ethiopianorthodox.org

ትዮጵያ ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ ለክሱ ፡ ስለሚሰጠው ፡ መልስ ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ ጉባኤ ፡ ተደርጎ ፡ በጉባኤው ፡ የተሰበሰቡት ፡ እሳቸው ፡ በአላፊነታቸው ፡ ሊናገሩት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አሳብ ፡ አዘጋጅተው ፡ ቢያቀርቡላቸው ፤ እኛ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ እንዲህ ፡ ብለን ፡ ብንናገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚያ ፡ በእኛ ፡ አድሮ ፡ የሚናገረው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከማቴዎስ ፡ ወንጌል ። „አሳልፈው ፡ በሰጧችሁ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ እንደምትናገሩ ፡ አታስቡ ፤ የምትናገሩት ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በናንተ ፡ አድሮ ፡ የሚናገረው ፡ ያባታችሁ ፡ መንፈስ ፡ ነው„ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ጠቅሰው ፡ ተናግረው ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እርሳቸው ፡ ይህን ፡ ጥቅስ ፡ ማስረጃ ፡ አድርገው ፡ ቢያቀርቡም ፡ በጉባኤው ፡ ለምክር ፡ የተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ ያቀረቡትን ፡ አሳብ ፡ እንዲናገሩ ፡ ማሳሰባቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ።

ምክሩ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዳኞች ፡ ሔደው ፡ በቀረበባቸው ፡ ክስ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ በምክር ፡ በተወሰነው ፡ አሳብ ፡ ሳይሆን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በገለጸላቸው ፡ መሠረት ፡ በተናገሩት ፡ ቃል ፡ ክሱን ፡ ፍሬ ፡ የሌለው ፤ አድርገው ፡ ቀንቷቸው ፡ ተመልሰዋል ።

እንዲሁም ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ ከማኅበሩ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በመጠጥ ፡ ምክንያት ፡ አእምሮውን ፡ አጥቶ ፡



የገዛ ፡ ራሱን ፡ ለመግደል ፡ አስቦ ፡ በመካከሉ ፡ በገላጋይ ፡ ብርታት ፡ ከዳነ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ወንጀል ፡ ተከሶ ፡ ወደሳቸው ፡ ዳኝነት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ አመዛዝነው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንኳን ፡ አዳነው ፤ ለምን ፡ ዳነ ፡ ተብሎ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ አይገባም ፡ ብለው ፡ አሰናበቱት ፤ ሰውየውም ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ አሳብ ፡ ምክር ፡ ሆኖት ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ጠባዩን ፡ ለማሻሻል ፡ ችሏል ።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ተወክሎ ፡ የበላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሆኖ ፡ ስለነበረ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጠላት ፡ በወራሪነት ፡ በያዘች ፡ ጊዜ ፡ የጠላትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ገዥነት ፡ ሳያውቅ ፡ ቆይቶ ፡ በኋላ ፡ ፖሊቲካ ፡ አሸንፎት ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ስለዐወቀለት ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቆንስል ፡ ሊኖር ፡ አይገባምና ፡ ቆንስላው ፡ እንዲዘጋ ፡ (ባንዲራው) ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማውም ፡ እንዳይሰቀል ፡ ብሎ ፡ ስለአዘዘ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ ስደተኞችና ፡ ምእመናኑም ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ አድርገው ፡ ሳለ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ መጥተው ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ምእመናን ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ ቆርጣችሁ ፡ የምታዝኑት ፡ የኢጣሊያን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መሆን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ዐወቀ ፡ ብላችሁ ፡ ነው ? ፤ ነገር ፡ ግን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐላወ ቅሁለትም ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ቀሪ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቆርጥ ፡ አይደለም ፡ ሲሉ ፡ አጽናንተው ፡ ተናግረው ፡ እንደነበረ ፡ አይዘነጋም ። የብፁዕነታቸውም ፡ ንግግር ፡ ሳይዘገይ ፡ የሰው ፡ ማወቅ ፡ ተሽሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላወቅሁለትም ፡ ያለ፡እንደሆነ፡ የተባለው፡ ቃል ፡ ከብሮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የነፃነት ፡ ፍጻሜ ፡ ለማየት ፡ ተችሏል ።

እንግሊዞች ፤ ኢጣሊያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያላትን ፡ ሙብት ፡ ዐውቀናል ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ በገዳሙ ፡ ተሰቅሎ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ለማውረድ ፡ መጥተው ፡ እርሰዎ ፡ ባሉበት ፡ እንዲወርድ ፡ ይምጡ ፡ ሲሉ ፡ ላኩባቸው ፤ መልእክተኞቹም ፡ ሰንደቅ፡ ዓላማውን ፡ ሊያወርዱት ፡ ነው ፡ ቢሏቸው ፡ „አሁን ፡ ጊዜው ፡ ፈቅዶ ፡ ቢያወርደው ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ጊዜው ፡ ሲፈቅድ ፡ ያወጣዋል ፡ ይሰቅለዋል ፡ ተዉት ፡ ያውርደው ፤ እኔም ፡ በጸሎት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ አልወጣም,, ብለው ፡ ትንቢት ፡ ተናግረው ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ አል ቀረም ፡ ፋሽስቶችና ፡ እንግሊዞች ፡ ጦርነት ፡ በነሡ ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞች ፡ አውርደውት ፡ የነበረውን ፡ የኢት ዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ራሳቸው ፡ ሰቀሉ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ያለ፡ፈቃደ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ የማይፈጸም ፡ መሆኑን ፡



በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ ያምኑ ፡ ነበር።አቡነ ፡ ዮሳብና ፡ ሌሎች ፡ ግብጻውያን ፡ መነኰሳት ፡ ለፓትረያርክነት ፡ ሹመት ፡ እንዲመረጡ ፡ በድምፅ ፡ አሰጣጡ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ነበረችበት ፡ አንደኛው ፡ እሳቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ይምረጡ ፡ ቢባሉ ፡ እኔ ፡ ሁሉንም ፡ ዐላውቃቸውም ፡ የማላውቀ ውን ፡ ብመርጥ ፡ ምርጫው ፡ ልክ ፡ አይሆንም ፡ የከህ ናት ፡ አለቃ ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የወደ ደውን ፡ ይምረጥ ፡ ሲሉ ፡ ድምፅ ፡ ሰጥተዋል ።

በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ. ም . በተደረገው ፡ የጳጳስነት ፡ ምርጫ ፡ የበቁ ፡ ሆነው ፡ በመገኘታቸው ፡ ለመመረጥ ፡ ቻሉ ። ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፵፭ ዓ. ም. ሐምሌ ፡ ፲፰፡ ቀን ፡ በእስክንድርያው ፡ ፓትረያርክ ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ጳጳስ ፡ ዘጎ ንደር ፡ ተብለው ፡ ተሾሙ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. መስ ከረም ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ግሽን ፡ የእመቤታችንን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ ቀድሰው ፡ በዐውደ ቱም ፡ ላይ ፡ ጸሎት ፡ አድ ርሰው ፡ የመጨረሻውን ፡ ቡራኬ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ታመው ፡ ጥቅምት፡ ፩፡ ቀን ፡ በ፸፩ ፡ ዓመት ፡ ከምስት ፡ ወር ፡ ዕድሜያቸው፡ከዚህ፡ዓለም፡በሰላም፡ተለዩ።

እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ እውነተኛ ፡ ጻድቅ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ሲለዩ ፡ ጉዳቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሁሉም ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብና ፡ የኒህ ፡ የደግ ፡ አባት ፡ ስምና ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ተረስቶ ፡ እን ዳይቀር ፡ በማሰብ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ ችሮታ ፡ እንዲሁም ፡ የመከራ ፡ ተካፋዮቻቸው ፡ በነበሩት ፡ የኢየሩሳሌም፡ስደተኞች ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ መታሰቢያ ፡ በሆነው ፡ በመንበረ ፡ ፀባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ በዐውደ ፡ ምሕረቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይህን ፡ መታሰቢያ ፡ በገንዘባቸው ፡ አሠርተው ፡ አቁመውላቸዋል ።

Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org